# የጆርጅያ መሪ-ድንጋዮች (The Georgia Guidestones)



በሃገረ ዩናይትድ ስቴትስ፣ ኤልበርት ካውንቲ የሚገኙት የጆርጅያ መሪ-ድንጋዮች ሃውልት። በቀላሉ ሁላችንንም የሚያግባባን የሃውልቱ ግርምት ጫሪነት መጠኑና አቀማመጡ ሳይሆን እላዩ ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች የሰፈሩት "ለዘመነ አመክንዮ" የሚሆኑ አስር መመርያዎች ናቸው። የሃውልቱ አሰሪዎች ማንነታቸው ይፋ እንዳይሆን ያስገነዘቡ ሲሆን፣ ይህም ተጠብቆላቸዋል። ይህ ህቡእ ቡድን ግን ስራውን ባከናወነላቸው አካል አማካኝነት ዓላማቸውን የሚያሥረዳ አጭር ፅሁፍ አሳትመዋል። ይህም ከግምትና መላምት ስራ ነፃ የሚያወጣ ሲሆን የሃውልቱ አሰሪዎች ከባእድ አምልኮ ሚስጥር ማህበራት፣ ከዓለም ቁንጮዎችና ከአዲስ የአለም ስርአት አጀንዳ ጋር ያላቸውን ትስስር ፍንትው አድርጎ ያሳያል።


ሃውልቱ ረዥም እድሜ እንዲኖረውና መልእክቱን በፍልስፍና፣ በፖለቲካዊና በከዋክብት ቆጠራ ወዘተ. አማካኝነት እንዲያስተላልፍ ተደርጎ ነው የተሰራው። በዙርያው አራት ድንጋዮች ያሉ ሲሆን እነዚህ ላይ በስምንት ቋንቋ፡ በእንግሊዘኛ፣ ስፓኒኛ፣ ስዋሂሊኛ፣ ሂንዲ፣ እብራይስጥ፣ ዓረቢኛ፣ ቻይኒኛ እና ራሽያኛ አስር የመኖር ህጎች ሰፍረውባቸዋል። ከሃውልቱ ጫፍ ላይ ባለው ድንጋይ ላይ ደሞ በአራት ቋንቋዎች፡ በባቢሎን፣ በክላሲካል ግሪክ፣ በሳንስክሪት እና በግብፅ ሂሮግሊፎች (የጥንት ስእላዊ ፅሁፎች) አጠር ያለ መልእክት ሰፍሮባቸዋል። እነዚህ የኋለኞቹ አራት ጥንታዊ ቋንቋዎች ለሚስጥር ማህበራቱ ባእድ አምልኮ ጋር በተያያዘ ሰፊ ቦታ እንዳላቸው ልብ ማለት ያስፈልጋል።

አራቱ ግዙፍ ድንጋዮች አቀማመጣቸው ከፀሃይ ኡደት ጋር የተጣመረ ነው። ከማህል ላይ የቆመው ድንጋይ ልዩ የሚያደረግ ሁለት ባህርያት አሉት፡- አንዱ



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message


በማህሉ ከደቡብ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ቀዳዳ ያለው ሲሆን በዚህ ቀዳዳ ሁል ግዜ ሰሜናዊው ኮከብ ይታያል። ሁለተኛው ፀሃይ ከምድር በምትርቅበት ግዚያት (በበጋ እና ክረምት ሶሊስታይስ) እና በአመት ሁለቴ ቀንና ማታ እኩል በሚሆኑበት ግዜ (ኢኲኖክስ) ፀሃይ የምትታይበት ጠባብ ቀዳዳ አለው።




ከሃውልቶቹ ስር ጉዳዩን የሚያብራራ ድንጋይ ተነጥፏል። በተጨማሪም ከስሩ የግዜ መቁጠርያ እንደተቀበረ ይናገራል።



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message




ይህ የተነጠፈው ድንጋይ ሲሆን፡- ትንሽ ስለ ድንጋዮቹ የሚያብራራ ሲሆን ደራሲውን (በብእር ስም)፣ ስፖንሰሮቹን እና የግዜ መቁጠርያ ሳጥን መቀበሩን ይናገራል፡፡ የሚከፈትበትን ግዜ ባዶ ትቶታል፡፡
እንዲህ ሃውልቶችን ከከዋክብት ቆጠራ ጋር በማያያዝ የሚስጥር እውቀት የሚሉትን ማስቀመጥና ማስተላለፍ ከጥንታውያን ግብፅ፣ ግሪክና ድሩድ እምነቶች የወረሱት ነው፡፡

**አስርቱ መመሪያዎች፡-** ለአዲስ የአመክንዮ ዘመን new Age of Reason መመርያ እንዲሆኑ ያስቀመጧቸው አስር ትእዛዞች እንደሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የሰው ልጆችን ከተፈጥሮ ጋር ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ከ500,000,000 በታች ማድረግ፡፡
2. መራባትን በጥበብ መምራት - ጥንካሬና ብዝሃነትን መጠበቅ፡፡
3. የሰው ልጆችን ሂወት ባለው አዲስ ቋንቋ አንድ ማድረግ፡፡
4. የጋለ ስሜትን - እምነትን - ባህልን - እና ሁሉንም ነገሮች በተረጋጋ አመክንዮ መግዛት/መቆጣጠር፡፡
5. ሰዎችንና ሃገሮችን በማያዳላ ህግና ፍትሃዊ ፍርድ ቤቶች መከላከል፡፡
6. ሁሉም ሃገሮች በውስጥ ራሳቸውን እንዲገዙ በመፍቀድ ውጫዊ ግጭቶችን በዓለም ፍርድ ቤት መፍታት፡፡



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message

7. የማረቡ ህጎችንና እርባና ቢስ አስፈፃሚዎችን ማስወገድ።
8. ግላዊ መብቶችን ከማህበራዊ ሃላፊነቶች ጋር ሚዛን መጠበቅ።
9. እውነት - ውበት - ፍቅርን አክብር - ፍፃሜ ከሌለው ጋር ተጣጣም።
10. በምድር ላይ ነቀርሳ አትሁን - ለተፈጥሮ ቦታ ተው - ለተፈጥሮ ቦታ ተው።

እንደምታዩት ትእዛዛቱ የዓለም ህዝብ ቁጥር እጅግ እንዲቀንስ፣ አዲስ የአለም ቋንቋ መቀበልን፣ የዓለም ፍርድ ቤት መመስረትን፣ እና የሰው ልጅ እርባታን (ኢዩጀኒክስ) ነክ ጉዳይን ሁሉ ያነሳል። በሌላ አነጋገር ይህ ለአዲስ የአለም ስርአት ሞዴል (ብሉፕሪንት) ነው። ይህ የሴራ ታሪክ መላምት ወይም ፈጠራ አይደለም አፍጥጦና አግጦ የምናየው እውነታ ነው።

**ህዝብ ቅነሳ**

የመጀመርያው ትእዛዝ በተለየ መልኩ አስደንጋጭ ነው። እንደ ቀላል ነገር ዛሬ ባለው የዓለም ህዝብ ቁጥር በ7 ቢሊዮን ብናሰላው ከዓለም ህዝብ 92.9 መቶኛው ምድር ላይ ነቀርሳ ነው፣ መወገድ አለበት። ይህ ማለት ምድር ላይ ካሉት 14 ሰዎች 13[ቱ] መወገድ ያለባቸው ናቸው። ቁጥሩን ማሰላት ለአይምሮ ዘግናኝ ነው። *2012* በሚለው ፊልም ስንት ሰዎች ናቸው በሂወት የተረፉት? ብዙም አይደሉም። እነማን ናቸው? የምድሪቱ ባለ ፀጎች። ይህ ፊልም የአይምሮ ሙሊት (predictive programming) ስራ ይሆን?

የትዝዛዙ መጨረሻ፦ *በምድር ላይ ነቀርሳ አትሁን - ለተፈጥሮ ቦታ ተው - ለተፈጥሮ ቦታ ተው* በማለት ይገስፃል። ይህ የሰው ልጅ ምድር ላይ በሂወት መኖሩን ከነቀርሳ ጋር ማነፃፀሩ እጅ የሚረብሽ ነው። በእንዲህ አይነት የአይምሮ ቅርፀት የዓለምን ህዝብ ማጥፋት ቀላል ያደርገዋል። የዓለም ህዝብ ቁጥር መቀነስ የዓለም ቁንጮዎች ደጋግመው በኩራት የሚናገሩለት ግባቸው ነው፦

በ1988 የብሪታንያው ልዑል ፊሊፕ ሙቶ ዳግም ቢፈጠር የዓለምን ህዝብ የሚፈጅ ቫይረስ ሁኖ ዳግም ቢፈጠር ደስ እንደሚለው ተናግሯል። በቅርቡ ደሞ ቢል ጌት "ዛሬ የዓለም ህዝብ 6.8 ቢሊየን ሁኗል። ወደ 9 ቢሊየን እየሄደ ነው። በአዳዲስ ክትባቶች፣ ጤና አገልግሎትና፣ የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ላይ ከሰራን ይህ ከ10 ወይም 15 መቶኛ መቀነስ እንችላለን።" ብሎ ነበር። ከግብር ክፍያ ነፃ ተብለው በሚያቋቁሟቸው ፋውንዴሽኖች የሚስጥር ስብሰባ እኚህ ጉዳዮች ሰፊ ቦታ ይዘዋል። የራሳቸው ህትመት እንደሚከተለው ይዘግበዋል፦

> *"አንዳንድ የአሜሪካ ከፊት ያሉ ቢሊየነሮች ሃብታቸው እንዴት የዓለም ህዝብ ቁጥር እድገትን ማቀዝቀዝ እና በጤናና ትምህርት መሻሻሎችን ለማግኘት ሊጠቅም እንደሚችል ለመወያየት በሚስጥር ተሰባስበዋል።*
>
> *ስብሰባውን የተካፈሉ በጎ አድራጊዎች የማይክሮሶፍት አጋር-መስራች የሆነው ቢል ጌት በጠራው መሰረት ሲሆን ለለውጥ እንቅፋት የሆኑ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ እንቅፋቶችን ለመሻገር ሃይላቸውን ለማስተባበር ተወያይተዋል።*

*በአንድ የውስጥ አዋቂ መልካሙ ቡድን የተባለው እንደነ የአሜሪካ ሃብታሙ ቤተሰብ አባታዊው መሪ የሆነው ዴቪድ ሮክፌለር ትልቁ፣ ዋረን ባፌት፣ ጆርጅ*



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message

*ሶሮስ፣ ፋይናንስ አድራጊው ማይክል ብሉምበርግ፣ የሚድያው ቁንጮዎች ቴድ ተርነርና ኦፕራ ዊንፍሬ ተካፍለዋል።”* (The Sunday Times, May 24th 2009)

ሁለተኛው ትእዛዝ *“መራባትን በጥበብ መምራት - ጥንካሬና ብዝሃነትን መጠበቅ”* በቀጥታ ህግ አውጪዎች የቤተሰብ ክፍልን እንዲያስተዳድሩ ይጠይቃል። አንድ ቤተሰብ ሊኖረው ስለሚችለው ቁጥር መወሰን ይችላሉ ማለት ነው። “*...ጥንካሬና ብዝሃነትን መጠበቅ”* የሚለው ደሞ “ከተመረጠ ርቢ” ስራ ጋር ወይም የማይፈለጉ የማህበረሰብ ክፍሎችን መሃን ማድረግ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ የኢዩጀኒክስ (eugenics) ሳይንስ እየተባለ ይታወቅ ነበር፣ ናዚዎች የታወቁበት ዋና ተግባራቸው ሲሆን ፖለቲካዊ ኪሳራ ውስጥ የሚከት ቃል ሆኖ በግልፅ መጠቀም ቀረ። ይህ አዲስ ጭብጥ አይደለም። ፕላቶ ሪፐብሊክ በሚለው መፅሃፉ የሚከተለው ምክር ለተዋጣለት አገዛዝ ይለግሳል፡-

> *“ከቤታሁ አዳኝ ውሾች ንፁህ ዶሮ ዝርያዎች... አሏችሁ አንዳንዶቹ ከሌሎቹ የተሸሉ አይደሉምን? እናም ስታረቧቸው ሳትመርጡ ከሁሉም ነው፣ ወይስ ተጠንቅቃችሁ ከምርጦቹ ብቻ? ደሞም ከወጣቶቹ ነው ወይስ ካረጁት የምታረቡት ወይስ ከደረሱት? እንዲህ አድርጋችሁ ካላራባችሁ ዶሮዎቻችሁ፣ አዳኝ ውሾቻችሁ ይወርዱብናል ብላችሁ አትጠብቁም? ፈረሶቹና ሌሎቹ እንስሳትስ? ለነዚህስ ሌላ ደንብ ነው ያለው? እኚህ መርሆች ለሰው ልጆችም የሚሰሩ ከሆነ ታድያ መሪዎቻችን የላቀ ችሎታ ያላቸው ይሆኑ ዘንዳ ማሰብ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ...እስከተቻለው ከፍተኛ መጠን ድረስ ምርጦቹ ወንዶች ከምርጦቹ ሴቶች ጋር መሆን አለባቸው፣ መጥፎዎቹ ደሞ ከመጥፎዎቹ ጋር የሚገናኙበት እስከተቻለው ዝቅተኛ መጠን መውረድ አለበት። መንጋው የተቻለውን ያህል ፍፁም ማድረግ ከተፈለገ የመጀመርያዎቹ ልጆች ማደግ አለባቸው የሁለተኛዎቹ ደሞ ማደግ የለባቸውም። በተጨማሪም የጠባቂ (ወታደሮቹ) መንጋ ከመከፋፈል የፀዳ እዲሆን ከተፈለገ ደግሞ ይህ ርቢ የሚደረግበት መንገድ ከመሪዎቹ በቀር ማንም ማወቅ የለበትም። እናም የሆነ ብልህ ስልት መፈጠር ይኖርበታል ዝቅተኛው ሰው መሪዎቹን ሳይሆን እድልን የሚያወግዝበት ሁኔታ እንዲፈጠር። በጦርነት የበላይ ለሚሆኑት ወጣቶች ደሞ ክብርና ሽልማቶች ማግኘት አለባቸው፣ በተለይም ደሞ ይበልጥ ከሴቶች ጋር የሚገናኙበት መንገድ ሊመቻችላቸው ይገባል፣ ይህ የተቻለውን ያህል ልጆች እንዲያስገኙ ያደርጋል። የሚወለዱት ልጆች መንግስት በመደባቸው ወንዶች ወይም ሴቶች ወይም ሁለቱም የመንግስት ስራ ለሁለቱም እኩል ይገባልና ሰራተኞች ይወሰዳሉ።”*

**አንድ የዓለም መንግስት**

*“አንዳንድ ሰዎች እኛ ለዩናይትድ ስቴትስ ከሚበጁ ተግባራት ተቃራኒ የምንፈፅም የሚስጥር ቡድን አባሎች ናቸው ብለው ያምናሉ፤ እኔና ቤተሰቤን “ዓለም-አቀፋውያን” እና ከሌሎች ጋር በዓለም ዙርያ የበለጠ የተዋሃደ ሉላዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርአት -እንደውም ዓንድ አለም ለመገንባት የምናሴር አድርገው ይወነጅሉናል። ክሱ ይህ ከሆነ፣ ጥፋተኛ ነኝ፣ በዚህም ደሞ እኮራለው።”* (ዴቪድ



This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional.
Please use purchased version to remove this message

ሮክፌለር፡ *"Memoirs of David Rockefeller"* *ገፅ* 405) ከበርቴው ስለ ዓለም አቀፋዊ *ሴራው ሂወት ታሪኩን በፃፈበት መፅሃፉ ያስፈረው ነው፡፡*

*አብዛኞቹ የመሪ ድንጋዮቹ ትእዛዛት የዓለም መንግስት፣ የሰው ልጅ ሂወት ሁሉንም ገፅታዎች የሚቆጣጠሩ "ጥቂት አብርሆት ባገኙ" ሰዎች መገዛትን፣* እምነትን፣ ማህበራዊ ሃላፊነትንና ኢኮኖሚን ጨምሮ ማለት ነው የሚያዙ ናቸው፡፡ ይህ አዲስ ሃሳብ አይደለም ከጥንት ጀምሮ የሚስጥር ማህበራቱ ሲያጠነጥኑት የነበረ የሚስጥር ትምህርታቸው ነው፡፡ ማንሊ ፒ. ሃል በ1917 እንደሚከተለው ፅፎ ነበር፡-

*"ብዙሃን ሲገዙ፣ የሰው ልጅ በድንቁርና ይመራል፤ ቤተ ክርትያን ሲገዛ፣ በኋላ ቀር እምነቶች ይመራል፤ መንግስት ሲገዛ፣ በፍርሃት ይመራል፡፡ ሰዎች በመጣጣምና በመግባባት በአንድ መኖር ከመጀራቸው በፊት፣ ድንቁርና ወደ ጥበብ፣ ኋላ ቀር አመለካከት ወደ አብርሆት ያለው እምነት፣ ፍራቻ ደሞ ወደ ፍቅር መሸጋገር ይኖርባቸዋል፡፡ ሚሶነሪ እግዚአብሄርና ሰውን ለማዋሃድ የሚሻ ሃይማኖት ነው፣ ይህን የሚያደርገው ከሚስጥሩ ተቋዳሾቹን የዩኒቨርስ ታላቁ ገንቢን ስራ ግልፅ እይታ ማየት ከሚችሉበት ንቃተ ህሊና እንዲበቁ በማድረግ ነው፡፡ ከዘመናት ወደ ዘመናት ሲሸጋገር የኖረ ለሰው ልጆች የሚሆን ፍፁማዊ ስልጣኔ ርእይ አለ፡፡ በዚህ ስልጣኔ እምብርት እጅግ ሃያል የሆነ ዩኒቨርሲቲ ይቀመጣል በዚህም ሁለቱም ስለሂወት ሚስጥራት የሚያስረዱ መንፈሳዊውና ስጋዊ ሳይንሶች የፍልስፍና ሂወት ለመረጡ ለሁሉም በነፃ ትምህርቱ ይሰጣል፡፡ እዚህ እምነትና ዶግማ ቦታ አይኖራቸውም፤ ጥልቀት የሌለው ይወገድና ወሳኙ ብቻ ይቀራል፡፡ ዓለም ማፍራት በቻለችው ይበልጥ አብርሆት ያለው አይምሮ ባላቸው ትገዛለች፣ እያንዳንዱም ብቁ የሆነበት ቦታን ይይዛል፡፡"* (ማንሊ ፒ. ሃል *"The Secret Teachings of All Ages"*)

በሌላ መፅሃፉ ደግሞ ሃል ጥንታዊ የዓለም ምግስት ህልምን ያብራራል፡

*"የዓለም ዲሞክራሲ የታላላቆቹ ክላሲካል ፈላስፎች የሚስጥር ህልም ነበር፡፡ ከሰው ልጆች ግቦች ሁሉ ታላቅ የሆነውን ለመፈፀም የትምህርት፣ የሃይማኖት፣ እና የማህበራዊ ተግባራት ግባቸው ተግባራዊና ሁሉን አቀፍ ወንድማማችነት የሚያሥገኝ እቅዶችን ያወጡ ነበር፡፡ ዓላማቸውን ይበልጥ ተግባራዊ ለማድረግም፣ እኚህ ጥንታዊ ምሁራን በሆነ ረቂቅ ማሰርያ እራሳቸውን በወንድማማችነት ማህበር ያደራጁ ነበር፡፡ በግብፅ፣ በግሪክ፣ በህንድ እና ቻይና የንግስት ሚስጥራት (ሚስጥራዊ እምነቶች) ውልደታቸውን አገኙ፡፡ ከሚስጥሩ የተቋደሱ -ፈላስፋ- ቀሳውስት ማህበርም ተመሰረተ፣ እኚህም በማስተማር፣ በማማከር፣ እና የመንግስት ገዢዎችን በመምራት ያገለግሉ ነበር፡፡"* (ማንሊ ፒ. ሃል *"The Secret Destiny of America"*)

ሃውልቱ ከቆመበት 1980 ዓ.ም ጀምሮ ብዙ መላምቶች ሲዘነዘሩ ነበር፡፡ በውኋላ ላይ ስለሃውልቱ ሰሪዎቹ በብእራቸው ፅፈው መፅሃፍ አዘጋጅተውለታል፡- "The Georgia Guidestones Guidebook"በሚል ርእስ ባዘጋጁት ፅሁፋቸው በተደጋጋሚ ጥንታዊ የሚስጥር ማህበራት ፍልስፍናን አንፀባርቀዋል፡፡ ለምሳሌ ከፅሁፉ የተወሰዱትን የሚከተሉትን ማጣቀሻዎች እንይ፡-



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional.
Please use purchased version to remove this message

*አሁን የሰው ልጅ የአለም መንግስት ለመመስረት የሚያስፈልገውን እውቀት ይዟል። ይህ እውቀት በሰው ልጆች ንቃተ ህሊና ውስጥ በሆነ መንገድ እንዲሰርፅ መደረግ አለበት። በቅርብ ግዚያት ሰብአዊው ቤተሰብ ልብ መነካትና መጋል ይናርበታል፣ ሉላዊ የአመክንዮ አገዛዝን እንድንቀበል።*
*እየቀረበ ያለው ቀውስ የሰው ልጆች የዓለም የሕግ ስርአት... እንዲቀበሉ ያሥገድዳቸዋል።*
*አርማጌዶንን መተካት የሚችሉ አማራጮች አሉ። የሚተገበሩ ናቸው። ግን በምድር ላይ ካሉ ሃገራት የሚገኙ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ካልተባበሩ አይሆንም።*
*እኛ የጆርጅያ መራ-ድንጋዮች ስፖንሰሮች ውዥንብር ውስጥ ያለውን የሰው ልጆች ዋና ችግሮች ይበልጥ ትኩረት እንዲሰጣቸው የምንፈልግ የጥቂት አሜሪካውያን ቡድኖች ነን። ... አቋሞቻችን ልክ ናቸው ብለን እናምናለን።*
*...በጥቂቱም ቢሆን እየመጣ ያለውን የአመክንዮ ዘመን ያፋጥኑታል።*
*...ሁላችንም መጨረሻ የሌለው ትንሽዬ ግን ወሳኝ አካሎች ነን። የድንጋዮቹ ኮከባዊ አቀማመጥ፣ የሰው ልጅ፣ በተፈጥሮውና በመላ ዩኒቨርስ ተገልጦ እንደሚታየው፣ ከውጫዊ መርሆች ጋር መግጠም እንዳለበት ያመላክታል። (to be square with External principles...) መጨረሻ ከሌለው ጋር በመጣጣም መኖር አለብን።*
*ፅሁፎቹ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ለሰው ልጆች መከተል የሚገባቸው እርምጃዎችን ከዩኒቨርስ ጋር ሚዛኑን የጠበቀ (ኢኩሊብሪም) አካሄድን ያሳያሉ። መጨረሻ የሌለው ሁሉም ህይወት ያለውን ነገር ያቀፈ ነው፣ ትግልንም ጨምሮ፣ ግጭትንም፣ ለውጥንም፣ ይህም በእግዚአብሄር ነብስ ውስጥ ያለውን መናወጥ የሚያንፀባርቅ ነው።*
*እኛ (የሰው ልጆች) የመንፈሳዊው መልካሙና ክፉው በዚህ ዓለም የሚተውኑበት ዋና መሳርያ ነን።*
*በ1980 እኚህ ድንጋዮችን በምናቆምበት ግዜ የአለም አስጨናቂው ችግር የሠው ልጅ ቁጥርን መቆጣጠር የሚለው ነው። ከቅርብ ክ/ዘመናት ወዲህ ቴክኖሊጂና የተትረፈረፈ ነዳጅ ብልህ ከሆነው በላይ ወይም ዘላቂ ከሆነው በላይ የሰው ልጅ ቁጥር እንዲባዛ አድርገዋል።*
*እርባታችንን መቆጣጠር ባስቸኳይ ያስፈልጋል።*
*በዚህ ሁናቴ ርቢ ሙሉ ለሙሉ የግል ምርጫ ጉዳይ ሊሆን አይችልም።*
*ሃላፊነት የጎደለው የልጆች መውለድ ሁኔታ በህግ መገደብ አለበት። ለልጃቸው በቂ አቅርቦታ መሟላት የማይችሉ ጥንዶች ለጎረቤቶቻቸው ሸክም ከመሆን መታገድ አለባቸው። የማያስፈልጉ ልጆችን ወደ ታጨቀች ጆልባ ማምጣጥ ክፉ ነው። ለልጆቹም ፍትሃዊ አይደለም። ለሌሎቹ ኗሪዎችም ጎጂ ነው።*
*የሰው ልጆች ርቢን መቆጣጠር የሚያሥችል እውቀት በአሁኑ ግዜ አለ።*

**ደራሲዎቹ እነማን ናቸው?**

እኚህ የአመክንዮ ዘመን የሚሹት ጥቂት አሜሪካውያኝ እነ ማን ናቸው? ማንነታቸውን ባይገልፁም ሚስጥራቸውን ለተቋደሱት ግን ፍንጮችን ትተዋል።




1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message

ከሚስጥር ማህበራት ባእድ አምልኮ ዶግማዎች ጋር የተያያዙ ለመሆናቸው ጥያቄ የለውም ለምሳሌ:- *...ሁላችንም መጨረሻ የሌለው ትንሽዬ ግን ወሳኝ አካሎች ነን:: የድንጋዮቹ ኮከባዊ አቀማመጥ፣ የሰው ልጅ፣ በተፈጥሮውና በመላ ዩኒቨርስ ተገልጦ እንደሚታየው፣ ከውጫዊ መርሆች ጋር መግጠም እንዳለበት ያመላክታል:: (to be square with External principles...) መጨረሻ ከሌለው ጋር በመጣጣም መኖር አለብን::* የሚለው ጉዳይ ከላይ እንዳለው ከታችም ይገኛል ከሚለው የመጣ:: ወይም:- *እኛ (የሰው ልጆች) የመንፈሳዊው መልካሙና ክፉው በዚህ ዓለም የሚተውኑበት ዋና መሳርያ ነን::* ከጥንዳዊነት የክህደት ትምህርት ጋር የተያያዘው ይገኙበታል:: እኚህ ፅሁፎች ብቻ ደራሲዎቹ ፍሪሜሶኖች ወይም ሮዚክሩሽያኖች ወይም ሌላ የባእድ ትምህርት ተከታይ የሚስጥር ማህበራት ሰዎች እንደሆኑ በግልፅ ያስረዳሉ:: ግን ከዚህም የበለጡ ፍንጮች ይገኙበታል:: ለምሳሌ ሃውልቱ እንዲሰራ ያዘዘው ሚስጥራዊው አር. ሲ. ክርስትያን የተባለው ሰው ስም::

## አር. ሲ. ክርስትያን

እራሳቸው ባሳተሙት መፅሃፍ የሃውልቱ አሰራር ታሪክን ይነግሩናል:: ፊንድሌ የተባለው አርክቴክት ቢሮ ውስጥ በትክከለኛ ስሙ ሳይሆን ሮበርት. ሲ. ክርስትያን በሚል እንዲጠራ የፈለገ ግለሰብ ሃውልቱ እንዲሰራ እንዳዘዘ ይናገራሉ::




ስሙ ቅፅል ስም ከሆነ እንዲህ ሃውልቱ ላይ መቅረፅ ለምን አስፈለገ? ስሙ ሌላ ቁም ነገር ይኖረው ይሆን? በርግጥም አለው:: እውነትም ይሁን ሃሰት በሚስጥር ማህበራቱ አፈታሪክ መሰረተ የሮዚክሩሽያን የሚስጥር ማህበር መስራች የሆነው ግለሰብ ክርስቲያኝ ሮዜ ክሮስ እንደሚሰኝ ይናገራሉ:: ይህ ሃውልቱን ከሮዚክሩሳውያን ጋር ከሚያገናኙ ብዙ ነገሮች አንዱ ነው::

## ሮዚክሩሳውያን

ሮዚክሩሳውያን የሚታወቁባቸው ከ17ኛው ክ/ዘመን ወዲህ ያሳተሟቸው ሶስት ማኒፌስቶዎች (መግለጫዎች) አሏቸው:: Fama Fraternitatis Rosae Crucis, Confessio Fraternitatis እና Chymical Wedding of Christian Rosenkreutz ይሰኛሉ:: እኚህ ማንነታቸው ባልገለፁ ሰዎች የቀረቡ ስራዎች በሚስጥር የተከበቡና አጠቃላይ ህብረተሰቡን ከሮዚክሩሳውያን ፍልስፍና ያስተዋወቁ ናቸው:: በተጨማሪም በምድረ አውሮፓ ታላቅ የፖለቲካዊና ምሁራዊ አቀማመጥ





1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message

መቀየርንም የሚያበስሩ ነበሩ፡፡ከዚህ ቀጥሎ ወድያው ዘመነ አብርሆት ተከተለ፣ ይህም ከፊውዳል ነገስታት መውደቅ ቃር አብሮ የመጣ ነበር፡፡ የጆርጅያ መሪ-ድንጋዮችም ከማኒፌስቶዎቹ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ይመስላል፡፡ ሚስጥራዊ የሆነ ድባብ በመፍጠር ስለ ታላቅ ሽግግር ይናገራሉ፡፡

ዘመነ አመክንዮ

ተደጋግሞ ዘመነ አመክንዮ የሚለው ይጠቀሳል፡፡ የታወቀው ሮዚክሩስያዊ ከነበረው ከቶማስ ፓይኔ ስራ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆን?




*"The Age of Reason: Being an Investigation of True and Fabulous Theology"* የሚለው ዳይስቲካዊ (በፈጣሪ የሚያምን ግን በሰው ልጆች ሂወት እጁን አያስገባም የሚሉት እምነት) የሚከተል የምርምር ፅሁፉ ሲሆን የተደራጀ ሃይማኖትን የሚያወግዝና የመፅሃፍ ቅዱስ ትክክለኛነትን የማይቀበል ስራ ነው፡፡ መርሆቹ በራእይ ከተገለፁ መርሆች ምትክ አመክንዮን ይጠይቃል፣ ይሕም አመለካከት በድንጋዮቹ ተካዮች የሚደገፍ ነው፡፡ ቶማስ ፓይኔ ሮዚክሩስያዊ ስለመሆኑ የታወቀ እውነት ነው፡፡

*"የሮዚክሩሺያዊ ወንድማማችነት በአሜሪካ ከመጀመርያው የአሜሪካ አብዮት በፊት ነበር፡፡ በ1774 የታላቁ የሶስቱ መማክርት (የወንድማማችነቱ ዋና አስተዳዳሪዎች) ቤንጃሚን ፍራንክሊን፣ ጆርጅ ክሊመር እና ቶማስ **ፓይኔ ነበሩ**፡፡"* (The Fraternitas Rosae Crucis, soul.org)

**ማንሊ ፒ. ሃል** *"The Secret Destiny of America"* **በሚለው መፅሃፉ ቶማስ ፓይኔን እንደሚከተለው ይገልፀዋል፡-**

*"ስለ ቶማስ ፓይኔ ጆርጅ ዋሽንግተን በሰይፉ ለአሜሪካ ቅኝ ግዛቶች ካበረከተው አስተዋፅኦ በላይ ቶማስ ፓይኔ በብእሩ አበርክቷል ተብሎለታል፡፡ የመንግስት፣ የሃይማኖት እና ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ዳግም መደራጀት ብቻ ነው ቶማስ ፓይኔ እንደታየው ፍፁም ስርአት ሊያመጣን የሚችለው፡፡"*

ይህ የሃውልቱ ሰሪዎች ሮዚክሩሽያኖች አልያመ የሮዚክሩሽያን መአርጎች በውስጣቸው ያካተቱ ፍሪሜሶኖች የሰሩት እንደሆነ ሌላው ማሳያ ነው፡፡

ከዚህም በላይ ነገሮችን ግልፅ ለማድረግ ይመስላል የጆርጅያ መሪ-ድንጋይ መፅሃፍ ፀሃፊዎች ጆ ፊንድሌ ትልቁ የሃውልቱ ቀራጭ ድርጅት ፕሬዚደንት ሜሶን እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በዮርክ ራይትና ስኮቲሽ ራይት 32ኛ መዓርግ ላይ እንደሆነ



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message

ጠቅሰዋል፡፡ ለዚህ ይሆን ሃውልቱን እንዲገነቡ መጀመርያውኑ በድብቆቹ ሰዎች የተመረጡት?

*መደምደምያ*

የጆርጅያ መራ-ድንጋዮች ዓለም አካሄዷን እንድትለውጥ የሚጠይቁ ዘመናዊ የሮዚክሩሻውያን ማኒፌስቶ/መግለጫ ነው፡፡ የዛሬና የነገን ዓለም ቅርፅ የሚያሲዙ ሚስጥራዊ ሃይሎችን ለማወቅ ሃውልቱ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ የሚስጥር ማህበራትን፣ የዓለም ቁንጮዎችን እና የአዲስ የአለም ስርአት አጀንዳን ያስተሳስራል፡፡ የዓለም መንግስት እንዲኖር፣ የህዝብ ቁጥጥር እንዲደረግ፣ የስነ አካባቢያዊ ፅንፈኛ ተሟጋችነት የሚደረጉት ግፊቶች ዛሬ በመገናኛ ብዙሃን በየእለቱ የሚወሱ ርእሰ ጉዳዮች ሁነዋል፡፡ ሃውልቱ በሚቆምበት በ1981 እንደዛ አልነበሩም፡፡ ወደ ግባቸው ምን ያህል እንደተቃረቡ አያሳም?

*መሬትን ለመንከባበከብ መመርያዎቹ ትርጉም ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ግን በደራሲዎቹ ምናባዊ (አይዲያሊስቲክ) ፅሁፍና በአካል በህዝብ ላይ የሚተገበሩበት ፖሊሲዎች -ስልጣኝ በተጠሙ ስግብግብ ፖለቲከኞች- የዓለማት ያህል ልዩነት አለ፡፡ የድንጋዮቹ መመርያዎች እጅግ ብዙ ግለሰባዊ (ሃይማኖታዊና ኢኮኖሚያዊ) ነፃነቶች እንዲጣሱና አብርሆት ያላቸው መንግስት ገዢዎች እንዲቆጣጠሯቸው ይጠይቃሉ፡፡ ከዓለም ህዝብ 92.9 መቶኛው ይቀነስ የሚሉትን ማውራትም አያስፈልግም፣ ከቁንጮዎቹ እንደማይነካ የጣወቀ ነው፡፡ በሚኖሩበት ሃገረ አሜሪካ መስራች አባቶቹ የፃፉት ህገ መንግት "በህዝቡ ለህዝቡ" የሚለው መርህ ምን ዋጠው? ወይስ ህዝቡን መሸርሸርያና የነበረውን ማህበራዊ ስርአት መናጃ ስልት ነበር? ይሄ ሁሉ የዲሞክራሲ ቅንብር አምባገነናዊ፣ ሕብረተሰባዊ አንድ የዓለም መንግስት እስኪመሰረት መሸጋገርያ ነበር? ለምድን ነው የዓለም ህዝቦች በዲሞክራሲያዊ መንገድ የማይወያዩበት? ለነገሩ ቁንጮዎች በሚድያዎቻቸው በኩል የሕዝቡን ይሁንታ ማምረት ይቻላቸዋል፡፡ ግን ይህ ሁሉም ላይ ላይሰራ ይችላል…*



1-2-3 FileConvert This PDF is Created by trial version of 123File PDF Professional. Please use purchased version to remove this message